# ስልጠና እና የሥራ ጥናቶች

**የመዋለ ሕጻናት ምንጭ ለመዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅራቢዎች የተለያየ ስልጠናን ይሰጣል።**

የሲሲአር የስልጠና የጊዜ ምድብን ይመልከቱ

**ዋሽንግተን ስታርስ (የስቴቱ የስልጠናና ምዝገባ ሥርዓት)**

የዋሽንግተን ስቴት የስልጠናና ምዝገባ ሥርዓት (ስታርስ) በመዋለ ሕጻናት፣ በቅድመ ትምህርት፣ እና ዕድሜያቸው ለትምህርት ቤት ለደረሱ መዋለ ሕጻናት ውስጥ ለሚሰሩ ግለሰቦች የሚሰጥ የሥራ ማሻሻያ ስልጠና ሥርዓት ነው።

በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ ያሉ የሥራ ፈቃድ ያላቸው የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅቢዎች የ20 ሰዓት መሠረታዊ የስልጠና ትምህርትንና በየዓመቱ የ10 ሰዓት ተከታታይ የስልጠና ትምህርትን መውሰድ ይጠበቃባቸዋል። የ20ውን ሰዓት መሠረታዊ ስልጠና በዋሽንግተን ስቴት ከተፈቀደለት አሠልጣኝ፣ ድርጅት ወይም የማህበረተሰብ ወይም የቴክኒክ ኮሌጅ በኩል ሊገኝ ይችላል። እነኝህ አስፈላጊ ነጥቦች ሁሉንም የቤተሰብ መዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅራቢዎችን፣ ዕድሜያቸው ለትምህርት ቤት ለደረሱ መዋለ ሕጻናት ተቆጣጣሪዎችን፣ ዕድሜያቸው ለትምህርት ቤት ለደረሱ መዋለ ሕጻናት የሥራ ቦታ አስተባባሪዎችን፣ የማዕከላት ዲሬክተሮችን፣ የፕሮግራም ተቆጣጣሪዎችንና የመምሪያ ሠራተኞችን ይመለከታሉ። የመዋለ ሕጻናት ምጮች የስልጠና የጊዜ መደብ በእኛ የሩብ ዓመታዊ ጋዜጣ ላይ ተዘርዝሯል።

**ስታርስ ደረጃ ቁጥር 1**

የሥራ ፈቃድ በተሰጠ በ7 ቀናት ውስጥ ወይም በመዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅራቢው ለሥራ ከተቀጠሩ በኋላ የአገልግሎት አቅራቢ መግለጫ ቅጽ ለዋሽንግተን ስታርስ መቅረብ አለበት።

**ስታርስ ደረጃ ቁጥር 2፣ የ20 ሰዓት ስልጠና**

ይህ ስልጠና የሥራ ፈቃዱ በተሰጠ ወይም ሥራ በተቀጠሩ በመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ውስጥ መጠናቀቅ አለበት። በ20ው ሰዓት ኮርስ ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት *An Adult Sized Guide to Child Sized Environments* በተባለው የስቴት የመመሪያ መጽሐፍ መሠረት ሲሆን መጽሐፉ ከዋሽንግተን የሥራ ፈቃድ አስፈላጊ ነጥቦች አባሪ የሚሆን ነው። የ20ው ሰዓት ኮርስ የተዘጋጀው በተለያዩ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት እንዲሰጥ ሆኖ ነው። የቅድመ የልጅነት-ጊዜ ወይም ዕድሜያቸው ለትምህርት ቤት ለደረሱ መዋለ ሕጻናት ከዚህ በፊት ስልጠናውን ያደረጉ አገልግሎት አቅራቢዎች የአገልግሎት አቅራቢ መግለጫ ቅጽ በመሙላትና አስፈላጊ የሆኑትን ሰነዶችን በማቅረብ ከስታርስ የትምህርት ግዴታ ነፃ ለመሆን ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። አገልግሎት አቅራቢው ከትምህርት ነፃ የሚያደርግ መረጃ ካላቸው ከ20 ሰዓት መሠረታዊ ስልጠና ነፃ ናቸው። የሥራ ፈቃድ ሰጪዎችም በሥራ ልምድ መሠረት ከትምህርት ግዴታ ነፃ ለማድረግ ፈቃድ ሊሰጡ ይችላሉ።

የሲሲአር 20 ሰዓት ስልጠና የጊዜ መደብን ይመልከቱ

ስለ20 ሰዓት ስታርስ ስልጠና የኢንተርኔት ወይም ቪዲዮ አማራጮች መረጃ ለማግኘት (ቪዲዮው ለቤተሰብ መዋለ ሕጻናት ብቻ ነው) ክርስ ሎውን በ lowe@childcare.org ይመልከቱ።

**ስታርስ ደረጃ ቁጥር 3፣ የ10 ሰዓት ተከታታይ ትምህርት**

በያመቱ አገልግሎት አቅራቢዎች የ10 ሰዓት ተከታታይ ትምህርት ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት በዋሽንግተን መሠረታዊ የትምህርት ብቁነት ክፍሎች ላይ የተመረኮዙ ናቸው። ለማዕከላት ዲሬክተሮች፣ ወይም የፕሮግራም ተቆጣጣሪዎች፣ በያመቱ ከአሥሩ ሰዓቶች አምስቱ በአስተዳደር ትምህርት ላይ መሆን አለባቸው። እነዚህ የትምህርት ክፍሎች ብዙ የትምህርት ነጥቦች ሲኖሯቸው በተለያየ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት እንዲሰጡ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው።

የሲሲአር 10 ሰዓት የስልጠና የጊዜ መደብን ይመልከቱ

## ፈቃድ ያላቸው አሰልጣኞችና የማሰልጠኛ ድርጅቶች

የዋሽንግተን ስታርስ ስልጠና በዋሽንግተን ስታርስ ፈቃድ በተሰጠው አሰልጣኝ ወይም ድርጅት በኩል ሊደረግ ይችላል። በተጨማሪም አገልግሎት አቅራቢዎች በስታርስ ያልተፈቀደውን የኮሌጅ ኮርስ ወይም ስልጠና እንደ አስፈላጊው ስልጠና ሆኖ እንዲቆጠርላቸው የተከታታይ ትምህርት መግለጫ ቅጽን በመጠቀም ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ለዚህ ስታርስን ይጠይቁ ወይም ሌሎች ቅጾችን ይመልከቱ።

የመዋለ ሕጻናት ምንጭ ከስታርስ ፈቃድ ያለው የስልጠና ድርጅት ነው። በዋሽንግተን ውስጥ ያሉ የኮሚውኒቲ ወይም የቴክኒክ ኮሌጆችም ፈቃድ አላቸው። ከስታርስ ፈቃድ ያላቸውን አሰልጣኞች ወይም የማሰልጠኛ አድራሻዎች የተሟላ ዝርዝር ለማግኘት ስታርስን ይጠይቁ።

WAEYC - Washington Association for the Education of Young Children
(253) 854-2565x17
(800) 727-3107x17

## በተጨማሪም ይመልከቱ

የተልኮ ትምህርት
ወጪዎችና ስኰላርሽፕ
የመጀመሪያ እርዳታ፥ ሲፒአር እና ለኤችአይቪ ስልጠና
የማህበረተሰብ ስብሰባዎች